መመሪያ ቁጥር 04/2010

# ልውጥ ሕያዋንን በዝግ አጠቃቀም ለምርምር ወይም ለትምህርት ለማዋል የሚያስችል ልዩ ፍቃድ ለማግኘት የሚቀርቡ ማመልከቻዎች ይዘትን ለመወሰን የወጣ መመሪያ

ልውጥ ሕያዋንን በዝግ አጠቃቀም ለምርምር ወይም ለትምህርት ለማዋል የሚያስችል ልዩ ፍቃድ ለማግኘት የሚቀርብ የፈቃድ ጥያቄ ማመልከቻ ዋና ዋና ይዘትን መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ፤

የአካባቢ፣ ደን እና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር ስለደሕንነት ሕይወት በወጣው አዋጅ ቁጥር 655/2001 (በአዋጅ ቁጥር 896/2007 እንደተሻሻለው) አንቀጽ 25 መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "ልውጥ ሕያዋንን በዝግ አጠቃቀም ለምርምር ወይም ለትምህርት ለማዋል የሚያስችል ልዩ ፍቃድ ለማግኘት የሚቀርብ የፈቃድ ጥያቄ ማመልከቻ ይዘት መወሰኛ መመሪያ ቁጥር 04/2010" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ ልውጥ ሕያዋንን በዝግ አጠቃቀም ለምርምር ወይም ለትምህርት ለማዋል በሚቀርቡ ማመልከቻዎች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

3. **አጠቃላይ መረጃዎች**

ልውጥ ሕያዋንን በዝግ አጠቃቀም ለምርምር ወይም ለትምህርት ለማዋል የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን አጠቃላይ መረጃዎች መያዝ ይኖርበታል፤

1/ የአመልካች ስምና አድራሻ እንዲሁም ከሚሰራበት መስሪያ ቤት ጋር ያለው ግንኙነት፤

2/ ፕሮጀክቱን ለማቀድና ለመተግበር፣ እንዲሁም ለቁጥጥር፣ ለክትትልና ለደኅንነት ኃላፊነት ያለባቸው ሠራተኞች ስምና የሰለጠኑባቸው መስኮች፣ እንዲሁም ሌሎች የብቃት መመስከርያዎች፤ በተለይም የኃላፊው ሳይንቲስት ስምና ብቃት የሚያሳይ መረጃ፤

3/ ተቋማዊ ብቃትን የሚገልጹ መረጃዎች፤ እንዲሁም ከደረጃ I-III የደህንነት መጠበቂያ ካቢኔቶች፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከደረጃ I-IV የሆኑ የላቦራቶሪ ወይም



Ministry of Environment, Forest and Climate Change